# ጾመ ሐዋርያት

**የዘንድሮ ጾመ ሐዋርያት ከግንቦት 16 እስከ ሐምሌ 5**

**(Fast of the Apostles 24th May – 12th July)**

ከዓቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም የሐዋርያት ጾም ነው። የሰኔ ጾም ይባላል። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሔዳቸው በፊት የጾሙት ነው። ምእመናንም እነሱን ምሳሌ አድርገው ከጰራቅሊጦስ በበነጋው ጀምረው ይጾሙታል። ይህ ጾም በሕዝቡ ዘንድ የወታደር ጾም ይባላል። ለስብከተ ወንጌል «ዘመቻ» የተዘጋጁት ሐዋርያት በጾሙት ተምሳሊት፤ በድሮ ዘመን ወታደሮች ለዘመቻ ሲነሡ ወይም ከዘመቻ ሲመለሱ በተሳተ በተገደፈ ይቅር በለን ለማለት በቀኖና ይጾሙት ነበር ማለት ነው። ይህ ጾም በመባጃ ሐመር ከፍና ዝቅ ስለሚል የተወሰነ ቀን የለውም አንዳንድ ጊዜ ከአርባ ይበልጣል፤ አንዳንድ ጊዜ ከሠላሳም ያንሳል።